# የዘመኑ ምሁርና ኢትዮጵያዊነት

አገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ እንኳን እንደዚህ ሁላችንም በየፊናችን በዘመድ አዝማድ ፤ በጓደኝነትና በአበልጅነት ይባስ ብለንም በጎጥና በመንደር ተሰነጣጥቀን ሁሉም በየፊናው ከማን አንሼ እያለ በስመ ተቃዋሚነት የከሌ ቡድን ፤ የከሌ ፓርቲ ፤ የከሌ ድርጅት እያልን ዘጠኝ ትንንሽ ቦታ ተበጣጥሰንና ተሸንሽነን ባለንበት በዚህ አሳዛኝ ሁኔታ ላይ ተቀምጦ አገር ማዳን ይቻላል ማለት ከተረት ተረትነት አያልፍም ።

እንኳን በየፊናው ተነጣጥሎ ይቅርና በአንድ ላይ ሆነን በአንድ ድምጽና በአንድ አላማ ተሰባስበን ብንታገል እንኳን ፤ እቺን መከረኛና ምስኪን አገር እናድናለን ማለት ወደማይቻልበት ጊዜ እየደረስን እንደሆነ ጭፍን ካልሆንን በቀር ከማንም የተሰወረ አይደለም ።

ይህንንም ስል ወያኔ የማይበገርና የማይደፈር ነው ለማለት እንዳልሆነ ግልጽ እንዲሆን እፈልጋለሁ ። ነገር ግን ወያኔን ተንተርሰው ኢትዮጵያን ካንዴም ለሁሌም ከዓለም ካርታ ለማጥፋት በትጋት እየሰሩ ያሉት የዓለማችን ኃያላን መንግሥታትና ታሪካዊ ጠላቶቻችን የሆኑት የአረብ አረጎችን ጭምር መዋጋት ስለሚኖርብን ነው ።

ስለሆነም ዛሬ ከሐገሬ እቆረቆራለሁ የሚል እውነተኛ ዜጋ ካለ ከዚህ በታች ለማቀርበው እውነታ ትክክል አይደለህም በማለት ሊሞግተኝ ይችላል ። በኔ እይታ ግን እንዲያው ለመቃወም ያክል እንደዘመኑ የሰለጠነ ፖለቲካ አራማጆች ነን ባዮች ሰንካላና እርባና ቢስ ትንታኔ በማቅረብ እንደማይሞግተኝ እተማመናለሁ ።

ይህ መሆኑ እየተዋቀ ታዲያ ዛሬ በየ ሚዲያው የምንመለከተው እንደ እንጉዳይ የፈሉ በስመ ተቃዋሚነት የተደራጁ ቡድኖች በተለይም የተቃዋምሚውን ቡድን (ፓርቲ) እንመራለን የሚሉት በሐገር ቤትም ሆነ በውጪ ሐገር ሆነው ቡራ ከረዩ ባዮች ፤ ለሐገራችን መበታተንና መጥፋት ከወያኔ ባልተናነሰ ተጠያቂነት እንደሚኖርባቸውና ከተጠያቂነትም እንደማያመልጡ በቅድሚያ ላስገነዝባቸው እወዳለሁ ።

እነዚህን ቡድኖችና በውስጣቸው ያሉትን ግለሰቦች በሥም መጥቀሱ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም ። የነዚህን ቡድኖች ጠባይና በውስጣቸው የተሰገሰጉትን ግለሰቦች ታሪክ ባለፉት የትግል ዘመናትም ሆነ አሁን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ ጋር ተያይዞት ባለው የሞት የሽረት ግብግብ ላይ የሚያደርጉት አሉታዊ አስተዋጽኦ አበጥረን ስለምናውቀው ነው ።

ቡድኖች ፤ ፓርቲዎች ፤ ግለሰቦች ያጠፋሉ ይሳሳታሉ ነገር ግን ጥፋታቸውን አርመው ትግሉን ለመቀጠል ብሎም ለመምራትም ሆነ ለመመራት ቅንነትንና ሕዝባዊነትን ይጠይቃል ። ባሁኑ ሰዓት አንስተን መወያየት የምንሻው በሕዝብ ሥም ሕዝብን እየጎዱ ፤ በትግል ሥም ትግልን እያኮላሹ ፤ የቆየና የተበላሸ ሥመ ጥፉ ታሪካቸውን ፋይዳ ቢስ በሆነ የአስመሳይ ተሃድሶ ፤ ዘመናዊና ብልጣብልጥ ፤ አዲስ አይነት ትግል በሚል ሲያስተጋቡ እናያለን ። ይህ ጉዞ የሚያሳየን ነገር ካለ የቆዩትም ሆነ አዳዲስ የፖለቲካ ተዋንያን የጊዜውን ምሁር በፖለቲካ አለመብሰልና በምሁር ሥም የሐገራችንን ህልውና በፖለቲካ ሸቀጥ ችርቻሮ ላይ እንዳዋሉት ነው።

አዎ! ቃላት መደርደርና ማሳመር ያውቃሉ ፤ ከንፈር በመምጠጥ የየዋሁን ለሐገር አሳቢውን ስሜት በመንካት እንባውን በቃላት መሀረብ ሊጠርጉለት ይሞክራሉ ። አዎ! በመጨረሻው ለኢትዮጵያ ስለሆነ ኪስህን አራግፍ ይሉታል ። እናም ይሄ ሁኔታ እስከመቼ ድረስ? ብለን

መጠየቅና ባጠቃላይ ትግሉ ባሁኑ ጊዜ የገጠመውን ችግርና ዝንባሌ (Trained) የዘመኑ ምሁራን እያደረጉ ያለውን አሉታዊ ሆነ አዎንታዊ አስተዋጽኦ መመርመር ተገቢ ይሆናል።

ትግሉ ችግር ገጥሞታል ስንል የጠላታችን የወያኔን ብርታት ሳይሆን ኢትዮጵያዊ ነን የሚሉ ለሕዝብ ቆመናል የሚሉ በሕዝብ ሥም የሚምሉ ለትግሉ ደንቃራ የሆኑና ለሕዝባዊ ኢትዮጵያዊ ትግሉም ሀላፊነቱን የያዙ ለጥፋቱ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም ተጠያቂዎች እነዚሁ ምሁራን ነን ባዮች ስለሆኑ አሉታዊ ገጽታቸውን አንስቶ ማበጠር ይጠበቅብናል ።

ይህን አሉታዊ ገጽታቸውን አንስቶ መወያየትና ትግሉን ወዴት አቅጣጫ ሊወስዱት እንደፈለጉና ይህንንም አጋልጦ ለትክክለኛው መንገድ አልባት መስጠት ለትግሉ መስመር መያዝ ዋናው በር ከፋች ነው እላለሁ ።

በሥም የፖለቲካ ፓርቲ ነን ባዮች እራሳቸውን ምሁር አድርገው በሚገምቱ አጋሰሶች አስከብበው "በቆማጣ ቤት አንድ ጣት ብርቅ ነው" እንዲሉ ሆነና ፤ ባባዶ እግሩ እየሄደ አፈር ገፍቶ ፤ አፈር መስሎ ባስተማራቸው ጭቁን አርሶ አደር ላይ መዘማነንና መኩፈስ ፤ የእኔ አውቅልሀለሁ ባይነት ገደቡን አልፎ አገር እስከ መሸጥ ደረጃ ስለደረሰ ሊነገራቸው ይገባል ።

የኛ ምሁር ነን  ባዮች እራሳቸውን ከማንም በላይ ትልቅ አድርጎ የመመልከት አባዜ የተጠናወታቸው ነገር ግን ከአንድ ኢትዮጵያዊ ገበሬ በኩራዝ ጎጆ ውስጥ ከልጆቹና ከከብቶቹ ጋር በአንድ ክፍል ታጉሮ ኩርምት ብሎ ከሚኖረው ምስኪን ገበሬ ጋር ሲነፃፀሩ የሐገራችንን ፖለቲካ በተመለከተና በሐገር ፍቅር በጭራሽ የማይመጥኑት ፤ ከሱ እጅግ በጣም ያነሱ ብቻ ሳይሆኑ ልዩነታቸውም በቃል ወይንም በአሀዝ ሊተምን የማይችል መሆኑን ቢያውቁት ኖሮ ይህንን ያክል ባልተንጠራሩም ነበር ።

አዎ! የኛዎቹ ሊቆች ባሰባሰባቸው አገር አጥፊ ድርጅት ጥላ ስር ተሰባስበው ከምዕራቡ ዓለምና ከየአረቡ መንግሥታት በሚጎርፍላቸው የጥፋት ማራመጃ (Petro Dollar) ደረታቸውን አሳብጠዋል ።

እነሱም ባቅማቸው ከነሱ በታች ሆኖ የሚሰራ ታማኝ አገልጋይ የሆኑ ትርፍራፊ ለቃቃሚ የሬድዮና የድረ ገጽ አዘጋጆች ለመግዛት አስችሏቸዋል ። ያንንም የጥፋት የብዙሀን መገናኛ በመጠቀም ከስማቸው ቀጥሎ እንደ ሎቲ ተንጠልጥሎ የሚቀርብልልን (Dr) ፤ (PHD) ፤ (professor) ገለመሌ ተቀጥላ በማስቀመጣቸው ብቻ ያውቃሉ የሚል ግንዛቤ እንዲኖረንና እንድንቀበላቸው ትልቅ ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ ።

ስለሆነም ዶ/ር እከሌ ናቸው ፤ ፕሮፌሰር እከሌ ናቸው ፤ እሳቸውማ ያውቃሉ ፤ እሳቸው ካሉ መቀበል አለብን እንድንል የፍግ ዶክተሩም  የሶሻል ወርከሩ ፕሮፌሰር ተብዬውም የፖለቲካውም ሊቆች እኛው ብቻ ነን በማለት በኢትዮጵያ ፖለትካ ውስጥ አለከልካይ ገብተው ሲፈተፍቱና ሲያቦኩ ይውላሉ ።

በነሱ ቤት ያገራችንን የወቅቱን ሁኔታ ከነሱ በላይ የተረዳና ከነሱ በላይ መተንተን የሚችል የለም ፤ ለሁሉም ነገር መልስ እነሱ ካልሰጡበት አይሆንም ፤ የነሱን ትንተና ካልተቀበልን አገር የለንም ማለት ነው ፤ የችግሩ መፍትሄ ቁልፉ እነሱ ብቻ የሆኑ ይመስል ሲራቀቁብን ማየቱ ካማሰልቸት አልፎ እጅ ፤ እጅ እያለ እንደመጣ ቢያውቁት እንዴት በወደድናቸውና ባከበርናቸው ነበር ።

በጣም የሚያሳዝነው ነገር ቢኖር እነኚህ በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ ተቀምጠው ከኛ በላይ ላሳር እያሉ ሐገር በታችና አፍራሹን እያሞካሹና እየደገፉ የድካችንን ቀን በማራዘም ለወያኔ አሌ የማይባል እገዛ እያደረጉ መሆኑ ነው ።

በሌላ ወገን እራሳቸውን ወዳድ ከመሆናቸው የተነሳ ሳያውቁት ሳይሆን አውቀውት ወገናቸውን በረሃብ አለንጋ እያስገረፉት ነው ። አዎ! ምናልባት የነሱ እናትና አባት እነሱ ከሚያገኙት የባንዳነት ክፍያ ትንሽ ትንሽ ስለሚደጉሚቸው አልተጎዱ ይሆናል ፤ ነገር ግን የራሳቸው የስጋ ዘመድ የሚሆኑ እኀትና አክስቶቻቸው ዛሬ ከአውሮፓና ከአሜሪካ በእርዳታ መልክ የሚገባ ስንደና ዘይት ተመጽዋች መሆናቸውን መርሳታቸው ነው ።

በነገራችን ላይ እነዚህ ምሁር ነንና እድምጡን ባዮችን ስተች ጸረ ምሁር አቋም በመያዝ እንዳልሆነ እንድትገነዘቡልኝ እወዳለሁ ። ሥማቸው ተቀጥላ ስላለው ብቻ የፖለቲካውም ዶክተሮች ነን በማለት ለሐገራችን መፍትሄ ፈላጊ ከመሆን ይልቅ ለችግሩ አላስፈላጊ ቀዶ ጥገና እያደረጉ በመሆናቸው እንደሆነ ላሳስብ እወዳለሁ ።

ይህ የምሁር አምላኪነት ምንጩ ምን እንደሆነ ባይታወቅም አብዛኛው ኢትዮጵያዊ እነዚህ እናውቅልሀለን ባዮች በሚያመጡት ቅራቅንቦ በመከየፍ ሊሰጣቸው ከሚገባው ግምት በላይ በመስጠትና እናቱ ላይ ተንሰራፍተው እንዲቀመጡ በመፍቀዱ አውቆም ይሁን ባለማወቅ እራሱንና አገሩን መጉዳቱ ያሳዝናል ።

እነዚህ የዶክተርና የፕሮፌሰር ግሪሳዎች ለሐገራችን መፍትሄ ከመሆን ይልቅ እንቅፋት እየሆኑ ነው ። እነዚህ ምሁርነታቸውን ሊነግሩን የሚፈልጉ ተመፃዳቂዎች መፃፍ የሚያበዙ ነገር ግን ከጽሑፋቸው ጋር ምንም ግንኙነት በሌለው ጉዳይ ላይ የሥም ኰቲ እያንጠለጠሉ ብቅ የሚሉት ምናልባት በተማሩበት (particular subject) ከሌላው የበለጠና የላቀ እውቀት ሊኖራቸው ይችላል ፤ ነገር ግን የኢትዮጵያን ፖለቲካ በተመለከተ ግን ከላይ እንደጠቀስኩት ካንድ ተራ ኢትዮጵያዊ ገበሬ ወይም ካንድ መርካቶ ላይ ሸንኩርት ቸርችራ ከምትተዳደርና ከአንድ በቀን ሙያተኛነት ተቀጥሮ ከሚሰራ ኢትዮጵያዊ ቢያንሱ እንጂ እንደማይበልጡ ሊያውቁት ይገባል ።

በአብዛኛው እነዚህ ምሁራን ነን ባዮች በየመድረኩ ብቅ ብቅ እያሉ ነገር የሚያደፈርሱት አላማቸው እራሳቸውን ለማስተዋወቅና የሚፈልጉትን ለማግኘት በፖለቲካ አስታኮ እራስን ለገበያ ለማቅረብ የሚያደርኩት እርብርቦሽና ጨረታ እንደሆነ በግልጽ ይታያል ።

በየ ፖለቲካ ፓርቲ ተብዬዎች ስር ያሰባሰቧቸው የጥፋት ምሁራንና በጋሻ ጃግሬነት የሚያገለግሉ የሚዲያ ባለቤቶችን ጨምሮ በአንድ ላይ ግንባር ፈጥረው ዛሬ አገራችንን ለመበታተንና ለመቆራረስ ደፋ ቀና ሲሉ ይታያሉ ።

የበላይ አዛዦቻቸው የሆኑት ምዕራባውያንና የአረብ መንግሥታት በየ ሚዲያቸው ላይ የሚዘግቡትን የኦጋዴን ነፃ አውጪና የኦሮሞ ነፃ አውጪ ፍሬ ፈርስኪ ከጸረ ኢትዮጵያ አመለካከት የመነጨ መሆኑ እየታወቀ የኛዎቹ ድፍኖችም ያንን ተቀብለው ጆሮአችን እስኪደፈን በየ አለቱ ሲያናፉና ሲዘምሩ ስናይ እውነት እነዚህን ሆድ አደሮች እራሳቸውን ትልቅ አድርገው የሚመለከቱ ነገር ግን ከማንም በታች የሆኑ ፍጡሮችን እንዴት ለአገራችን የሚያስቡና የሚቆረቆሩ እውነተኛ ኢትዮጵያውያን ዝም ብለው ዘመናዮቹ እንዳሻቸው ባገራችን ጉዳይ ገብተው ሲያበራዩ ማየቱን አስቻላቸው? እውነትም ኢትዮጵያ ዛሬ ልጆቿ ክፉኛ እንቀላፍተዋል ለማለት ያስደፍራል ።

ወደድንም ጠላንም አድሜ ለነኚህ ተቃዋሚ ነን ባዮችና በስራቸው ለተሰባሰቡት የጥፋት ምሁሮች ፤ እንዲሁም ፍርፋሪ አጋባሽ ሚዲያዎች ፤ ዛሬ በምስራቅ ኢትዮጵያ የሚገኘው

EthioLion.Com

የኦጋዴን ክፍል ተቆርጦ ለሱማሊያ እንደሚሰጥ ነው ። ካልሆነም እንደ ኤርትራና ጅቡቲ እራሱን ከኢትዮጵያ ነጥሎ እንደመንግስትነት እንዲቆም እየተደረገ ነው ። የአረቡና የምዕርቡ ሚዲያ ሲያናፍሰው የኖዎቹም ተቀብለው ሲያራግቡት ማየትና መስማት የሐግሩ ጥፋት ለሚያንገበግበው እንዴት ልብ እንደሚያደማ መገመት አያስቸግርም ።

ከዚህ ቀደም በኢትዮ ላዮንና በደብተራው ድረ ገጽ ላይ አንድ አገር ወዳድ <u>“ እንዴት ዛሬም ፤ የገደለሽ ይብላ?”</u> በሚል ርዕስ ያቀረቡት ላይ ስለነዚህ የግንጠላ ቡድኖችና ስለወያኔ ሲገልጹ <u>“አህያ ካህያ ቢራገጥ ጥርስ አይሳበርም”</u> በማለት በአጭርና ግልጽ በሆነ አገላለጽ አስቀምጠውታል ። ትክክለኛ አባባልና አቀራረብ ነው ።

እነዚህ የግንጠላ ቡድኖችን በተመለከተ ከላይ የጠቀስኳቸው ጸሀፊ ምን መደረግ እንዳለበት ቁልጭ ባለና በግልጽ ቋንቋ ስለተነተኑት የኚህን ሰው ጽሁፍ እንድታነቡት ሳላሳስባችሁ አላልፍም ።

ታዲያ እነዚህ የተቃዋሚዎ ፓርቲዎች ፤ ምሁሮች ፤ ሚዲያዎች ፤ ከተገንጥዩና ካፍራሹ ጋር ሆነው የሚያጨበጭቡት ወያኔን የጎዱ ወይም የመቱ መስሏቸው ይሆን? ወይስ ወያኔ ለኢትዮጵያ መፈራረስ እየሰራ እንደሆነ ጠፍቷቸው?

ወያኔ ዛሬ ትግሬን ከቀረው የኢትዮጵያ ክፍል ገንጥሎ ለመሄድ አመቺ ጊዜ እየጠበቀ አይደለም ? ታዲያ እነዚህ ሊቆች “ኦጋዴን ፤ ኦሮሚያ” እያሉ የሚያላዝኑብን ግንጠላውን ለማጣደፍ? እንደነሱ ጩኸት የተቀረው ኢትዮጵያዊ አልተበደለም ፤ አልተጎዳም ሊሉን ይሆን? አድራጎታቸውና ስራቸውስ አሁን ወያኔ ከሚያራምደው የአፈራርሰው ፍልስፍና በምን ተለዩ? ወይንስ በእጅ አዙር ለወያኔ ነው የሚሰሩት?

የውጪው አለም እንደሆነ ዛሬ ኦጋዴንን ለማስገንጠል የሚያስችላቸውን ካርታና መሰል ቅድመ ዝግጅቶችን አስቀድመው የጨረሱት ጉዳይ  እንደሆነ ለሁላችንም ግልጽ ነው ። ታዲያ አሁን እነዚህ አነፍናፊዎች የሚያጎበጉቡት ለምን ግንጠላው አልተፋጠነም በሚል ቁጭት ነው ፤ ወይስ የሚሰሩትን ስለማያውቁ? ኢሊያም ያባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ በሚለው አጉል ተረት? የዘመኑ ምሁርና ኢትዮጵያዊነት ምን እንደሆነ ሊገባኝ አልቻለም ። አንባቢያን መልሱን ተመራምረው ከደረሱበት አላማቸው ካልገባን ሊያስተምሩንና ሊያስረዱን ይገባል ።

ድል ለኢትዮጵያ ሰፊው ሕዝብ !

የተባበረና የተቀነባበረ የሕዝብ ትግል ያቸንፋል !

ከአይምሮ ዳኛቸው

EthioLion.com